# ይህአባ(ኢህአፓ) እውነት አረጀ ? ? ?

(ትርሲትና ድላይ)

አረጀህ ይሉኛል። ማርጀትማ መች ይቀራል። ለእዚህ ማዕረግ ለመድረስ በወጣትነቴ የወረደብኝን መዓት ዓለም መዝግቦታልና ለእዚህ መበቃቴ ቢያስገርም አይደንቅም። አረጀህ መባሉንስ ያገኙሁት ሞቼ በመኖሬ አይደል። እንጅማ ስፈጠር ጀምሮ ሞቱንማ ደጋግሜ ሞቸዋለሁ። ህያውነቴን ግን ዛሬም በእርጅናዬ አረጋግጫለሁ። እርጅናማ ማዕረግ ነው። የእድሜ ባለፀጋ መሆን፣ ክብር፣ አንቱታን ማግኘት። የተመክሮ የልምድ ባለቤት፣ የምክር አባወራ መሆን። እርጅናማ ፀጋ ነው። ወላድ በድባብ ትሂድ እድሜ ለልጆቼ ለዚህ ማዕረግ በቅቻለሁ። ገና በልጅነት በለጋነቴ በመቃብር ውስጥ ያረጁ ልጆቼን አውቃለሁ። ያኔ እነርሱ ሞተው፣ ስቃይ መከራን ተቀብለው፣ ሰብዓዊነታቸውን አጥተው፣ ከሰውነት ወጥተው፣ በሞታቸው፣ በሥጋና በአጥንታቸው መኖሬንና፣ ለዛሬ ህያው መሆኔን ባያውጁልኝማ፣ ከሞትኩኝማ ቆይቻለሁ። ግና ደግሞ በሞታቸው ህይወትንም አግኝቻለሁ። የሚገርመው ግን ዛሬም በእርጅናዬ ለፍቅሬ ሲል ሟቹ፣ መብዛቱ ነው። በእርጅናዬ በውበቴ ተማራኪ፣ በትንቢቴና በህልሜ ተዋዳቂ፣ በምኞቴና በዝናዬ ተጨናቂ፣ በታሪኬና በክብሬ ተጠያቂ አለሁ የሚለኝና የሚዋደቅልኝ ዛሬም ድረስ በእርጅናዬም አለመንጠፉ ነው። እንጅማ ማርጀቴማ የት ይቀራል። የመኖሬስ ዋስትና አይደል? እርግጥ ነው ለእዚህ ማዕረግ ስበቃ ዛሬ አረጅተሃልና የሚሉኝ፣ ትናንትና ለዚህ እንዳልበቃ ገና ከመወለዴ ጀምሮ መወለዴን፣ መኖሬን የጠሉ፣ እንዳልኖርም ብዙ ጊዜ ደጋግመው የገደሉኝ ናቸው። አዎን! ዛሬ አርጀትሃል ባዮቼ ለዚህ ማዕረግ እንዳልበቃ ነበርና ያኔ ገና በልጅነቴና በለጋነቴ ሰውነቴን ከሰውነት ውጭ አድርገው፣ ሥጋዬን፣ አካሌንና ሥነ ልቡናየን በእጅጉ የጎዱኝ ፣ህልውናዬንም ሊያሳጡኝ ብዙ የደከሙ ባላንጣዎቼ ነበሩ። አዎን! ለዚህ ማዕረግ እንድበቃ ብዙ የሰው ህይወት ገብሬለሁ፤ ብዙ ደም ፈሶብኛል። አዎን! ሽህዎች ቆስለውብኛል፤ ሽህዎች ታስረውብኛል፣ሽህዎች አካላቸው ተተልትሏል። አዎን! የሽህዎች ደም በገጠሩና በከተማው በሞላ ተዥቅዥቋል። አዎን! ሽህዎች አካለ ጎደሎ ሆነውብኛል። ለክብሬ፣ ለዝናዬ፣ ለታሪኬ፣ ላልታጥፈውና በየጊዜው በሚሊዮኖች ለሚታደሰው ቃሌ ውድ ህይወታቸውን የሰጡኝ ሚሊዮኖች ናቸውና፣ ተመስገን ቃሌን ጠብቀው ለዚህ አብቅተውኛልና ልጆቼን ኢትዮጵያ ትዘክራቸዋለች። አዎን! የመኖሬ ምስጢሩስ ይሄ አይደል? እንጅማ ማረጀቴማ

የት ይቀራል? ለዚህስ ይበቃል መች ተብዬ? እርጅናማ ማዕረግ ነው። የዕድሜ ባለፀጋ መሆን፣ መከበር፣ አንቱታን መጎናፀፍ፣ እሰዬው! አረጀህ? ለመባል መብቃት። ታዲያ ይሄንንማ ይታደሉታል እንጅ ይታገሉታልን? ይህአባ አርጅቷል ይሉኛል ። ማረጀቴንና ለቁም ነገር መታጨቴን ያወቁት ገና በልጅነቴ እንደተፈጠርኩ መሆኑን አውቃለሁ። ዛሬ ለዚህ እንድበቃ ያደረሱኝ፣ ቢያድግ ቢሰፋ ብለው ሚሊዮኖች እንትፍትፍ ብለው የመረቁኝ፣ እስትንፋሴን በደም ያቀዩኝ፣ በአጥንታቸው የጠገኑኝ፣ ለወግ ለማዕረግ ያበቁኝ፣ ወጣቶች ወንድም ጋሽ፣ እናቶች አያኩራቴ ፣ መእመናን ምርኩዜ፣ አባቶች ጥላ ከለላዬ ያሉኝ፣ ያኔ በልጅነት/በወጣትነቴ ለሃገሬ ለኢትዮጵያ ትልቅ ነገር በመመኘቴ ነው። ይህአባ ባለ እድሜ ነኝና ለዚህም ደርሻለሁ። እንጅማ! ሚሊዮኖች እንደተንከባከቡኝና ተገን እንዳደረጉኝ ባላንጣዎችም አላጣሁም። ግና ደግሞ ዛሬ እርጅናዬን የሚያበስሩኝ ህያው በመሆኔ ነውና፣ ለህያውነቴ የከፈልኩት ዋጋ በመሆኑ አዎን! እርጅናዬን እኮራበታለሁ። እርጅናማ ማዕረግ ነው። የእድሜ ባለፀጋ መሆን፣ መከበር፣ ልምድና ተመክሮ የተገኘበት፣ ምክር የሚዘከርበት፣ አንቱታን የሚጎናፀፉበት ነውና እርጅናማ ይፈለጋል። ባላንጣዎቼ ሞቼ የመኖሬንና የእርጅናዬን ምስጢር በአወቁ ቁጥር ማንነቴን ይነግራቸዋልና ከእኔ በላይ ስለእኔ ብዙ ጊዜ ይጨነቃሉ። ከጭንቀታቸው የሚያወጣቸው ይመስላቸውና ኢህአፓ እኮ አርጅቷል ይሉና የመድፊያው ሀረግ ይጠፋባቸዋል። ዛሬ ከዚህ በላይ ሊያደርጉ አይቻላቸውምና እርጅናዬም ያሳስባቸዋል። እርጅናዬንም ደጋግመው ደጋግመው ለራሳቸው በማስማት ለጭንቀታቸው መድህን ያገኙ ይመስላቸዋል። ደጋግሜ በመገደሌና በመሞቴ እንዳልተርፍ ሆኜ ተጎድቻለሁና ዛሬ የህያውነቴን ሚስጢር ገና አልደረሱበትም። ታዲያ እኔ ምን ማድረግ ይቻለኛል ልባቸውን ያራራልኝ ከማለት ሌላ። እንጅማ እርጅናማ የት ተገኝቶ? ሞቼ የኖርኩት ህይወቴ ነውና በእድሜዬ ያገኘሁት ፀጋ ነው። ገናም የማቱሳላን እድሜ ይስጠኝ እላለሁ። እንጅማ እርጅናማ ማዕረግ ነው። የዕድሜ ባለፀጋ መሆን፣ መከበር፣ የልምድና የተሞክሮ ባለቤት፣ የምክር፣ የሽምግልና አባወራ መሆን። እንጂ እርጅናማ! የት ተገኝቶ።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር

እድሜና ጤና ለሁላችን! የከርሞ ሰው ይበለን!